**ዜና ዘገባ (የካቲት 30 ቀን፣ 2000 ዓ. ም.)**

**የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከአባ ገብረ መድህን ጋር ተጣሉ፣ አቡነ ሳሙኤልም በ ደህንነት የዓይን ቁራኛ ውስጥ ሆነው ክትትል እየተደረገባቸው ነው፣ የወያኔው ተላላኪ ሼህ ኤልያስ ሬድዋን ከሰልጣኑ እንዲነሳ የእስልምና እምነት አባቶች ጠየቁ፣ 3 አባቶችም በዚህ ሰ በብ በደህንነት ታፈኑ፣ በቤተ መንግስት ውጥረት ሰፍኗል፣ በዲላና ዓለማያ ተማሪዎች ተባረሩ ፣ ሁለቱ እድሜ ልክ ታገዱ፣ የወያኔው ግርማ ብሩ ዘብጥያ ወረደ »»»»»»»»»»»»»»»»»**

**ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ጣቢያ** ...............................

በኦርቶዶክስ እምነት እና በእስልምና መሪዎች ነን በሚሉ ሁለት የወያኔ ጉዳይ አስፈፃሚዎች ላይ ሰሞኑን ተቃውሞ ከየአቅጣጫው እየተነሳባቸው መሆኑን ከተለያዩ አካባቢዎች የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

የኦርቶዶክስ እምነት አባት ናቸው ተብሎ ከስደት ካሉበት ሀገር አሜሪካ ተጠርተው የሊቀ ጳጳስነት ማዕረግ ከተሰጣቸውና ከቤተክርስቲያኒቷ ህገ ደንብ ውጭ በጠመንጃ ኃይል የተረከቡት አባ ገብረመድን ሰሞኑን ከጳጳሳት ከፍተኛ ውግዘትና ተቃውሞ እየቀረበባቸው መሆኑን ለቤተክህነት ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገለፁ::

የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የሆኑት አባ ሳሙኤልን ጨምሮ ለጊዜው ስማቸው ያልተገለፁ አራት ጳጳሶች በአንድነት አባ ገብረመድህን በኦርቶዶክስ እምነት ስም እየፈፀሙ ያሉት አስነዋሪ ድርጊት በአስቸኳዩ እንዲገታ የሚያሳስብ ደብዳቤ ፅፈው የሰጡ ከመሆኑም ባሻገር በአካል ተገኝተው ይህንኑ መግለፃቸው ታውቋል ሲሉ እነዚሁ ወገኖች ገልፀዋል::

አያይዘውም እነዚሁ ወገኖች እንዳሉት ከሆነ አባ ሳሙኤልን ጨምሮ አራቱ ጳጳሳት አባ ገ/መድህን ከምዕመናን በተሰበሰበ ገንዘብ በየቤተክርስቲያኑ ግቢና አደባባይ ፎቶዬ ይለጠፍ ብለው ትዕዛዝ የሰጡትንና በትዕዛዛቸው መሠረት በሁሉም ቤተክርስቲያን የተሰቀለው ምስላቸው በእምነቱ በኩል የማያስኬድና የቤተክርስቲያኗን ደንብ የጣሰ በመሆኑ በአስቸኳዩ ከድርጊታቸው እንዲታቀቡና የተሰቀሉት ምስሎች ሁሉ ከየአደባባዩ እንዲነሱ የሚያሳስብና ለሚሊኒየሙ የሀመር መኪና ይገዛልኝ ብለው ያቀረቡት ጥያቄ ከአንድ የእምነት አባት የማይጠበቅ በመሆኑና ይህንንም ሀሳብ በመቃወም በደብዳቤና በአካል ንስሐ እንዲገቡ ጥያቄ ያቀረቡላቸው መሆኑንም አብራርተዋል::

ዛሬ የእምነቱ ተከታዮች በኑሮ ውድነት የተነሳ በከፍተኛ ችግር ውስጥ ተዘፍቀው እያሉ የመንፈሳዊ አባት ናቸው የተባሉት የወያኔው ተሿሚ አባ ገ/መድህን ፎቷቸው እንደ ፋሽቱ ደርግ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃ/ማርያም በየአደባባይ ይሰቀልልኝ ማለታቸው በጣም የሚያሳዝን እና የኃይማኖቱን ተከታዮች ልብ ያቆሰለ የአንድ ካድሬ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ስራ መሆኑን ያሳያል ሲሉ በርካታ ድርጊቱን የተከታተሉ ምዕመናን በንዴት ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

አልፎ ተርፎ እንደ ዘመናዊ ፖለቲከኞች ጥይት የማይበሳው መኪና አስገዝተ እየተጠቀሙ ከመሆኑም ባሻገር ሀመር መኪና ተገዝቶ ይሰጠኝ ማለታቸው ይበልጥ አለማዊ ሰው መሆናቸውን የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን የወያኔ ጉዳይ አስፈፃሚ በመሆናቸው ብቻ በቦታው ላይ ሊቀመጡ እንደቻሉ ያስመሰከሩበት ወቅት ላይ ደርሰናል ሲሉም እነኚሁ ምዕመናን ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

ዛሬ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ሳሙኤልን ጨምሮ አራቱ ጳጳሳት አባ ገ/መድህን እያደረጉ ያሉትን ተቃውሞ በይፋ ይጋፈጡ እንጂ 90 ከመቶው የሚሆኑት ጳጳሶች የእነ አቡነ ሳሙኤል ደጋፊዎች መሆናቸውን የገለፁት እነዚሁ ለቤተክህነት ቅርበት ያላቸው ወገኖች በተለይ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ሰውየው ማን አለብኝ በማለት በመቶዎች የሚቆጠሩ ካባ ለባሽ ደህንነቶች ተመልምለው እንዲሰለጥኑ አድርገው በነዚህ የደህንነት ኃይሎች እያስፈራሩ መሆናቸውንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በቅርቡም በአቡነ ሳሙኤልና ተከታዮቻቸው ላይ ዛቻና ስድብ እየሰነዘሩባቸው ከፍተኛ ወከባ ለመፍጠር ሙከራ እያደረጉ ቢሆንም ጳጳሶቹ አምላክ የፈቀደውን ለመፈፀም ዝግጁ ነን በማለት ማስፈራሪያውን እያጣጣሉት መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የእስልምና ምክር ቤት ምክትል ሊቀመንበር ሼህ ኤልያስ ሬድዋን የተባለው ግለሰብ የወያኔ ጆሮ ጠቢና ጉዳይ አስፈፃሚ በመሆኑ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ውግዘት እየደረሰበት መሆኑ ከእስልምና ምክር ቤት ውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

ሼህ ኤልያስ የተባለው የወያኔ ሹመኛ ካድሬ ወያኔ የሚፈልገውን ሁሉ በእስልምና እምነት አማኞች ላይ እየጫነ እምነቱን ለማጉደፍ እየተሯሯጠ መሆኑን የጠቀሱት ምንጮቹ ሰሞኑን የወያኔ ትምህርት ሚኒስቴር ያወጣውን መመሪያ በመቃወምና አቋም የወሰዱትን አባቶች በደህንነት ክትትል እንዲደረግባቸው መመሪያ ማስተላለፉንም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ሳይጠሩት አቤት ሳይልኩት ወዴት እያለ የሙስሊሙን እምነት ተከታዮችን በወያኔ በትር እየገረፈና እያሰቃየ ያለው ሼህ ኤልያስ የተባለው ሰው ትምህርት ሚኒስቴር ያወጣው ሕግ አግባብ ያለው ነው በማለት ከመከራከሩም ባሻገር ተፈፃሚ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርግ የነበረ መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ይህንኑ በመቃወም በመላው ሀገሪቱ ከሚገኙ የእስልምና እምነት ምክር ቤቶች ተውጣጥተው ባለፈው ሳምንት በአዲስ አበባ እስልምና ምክር ቤት ውስጥ ስብሰባ ያደረጉ ሲሆን፣ በዚህ ወቅት የትምህርት ሚኒስትር ያወጣውን መመሪያ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እንደሚቃወሙና ጭራሹንም እምነቱን የሚያዳክም እርምጃ በመሆኑ አጥብቀው እንደሚኮንኑ ባወጡት መግለጫ ላይ መግለፃቸውንም ምንጮቹ አብራርተዋል።

ይህ መግለጫ ከወጣ በኋላ ከአርሲ ተወክለው እንደመጡ የተነገረው 3 የእምነቱ አባቶች በሼህ ኤልያስ ትዕዛዝ ሰጪነት በደህንነት ተይዘው ወዳልታወቀ ስፍራ እንደተወሰዱ ምንጮቹ ገልፀው ምናልባትም ማስፈራሪያ ተሰጥቷቸው ሳይመለሱ እንዳልቀረ ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል።

ወያኔ ለ16 ዓመታት ሕዝቡን ለማዳከምና እንደልቡ ለመግዛት እንዲመቸው የተለያዩ የጥፋት ሴራዎችን ሲተገብር ቢቆይም አልበገር ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ አሁን ደግሞ በእምነት አሳብቦ በየትምህርት ቤቱ የሙስሊም ተማሪዎች እምነታቸውን እንዳይገልፁ የሚያሸማቅቅ ሕግ ማውጣቱ በእጅጉ አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ የእምነት ነፃነትን የነጠቀ በመሆኑ አጥብቀን ልንቃወም ይገባል ሲሉ የእምነቱ ተከታዮች አፅንኦት ሰጥተው እየገለፁ ይገኛሉ።

በወያኔ ጉዳይ አስፈፃሚ በሼህ ኤልያስ ሬድዋን በኩል ይኸው ሕግ ተግባራዊ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ቢሆንም በሙስሊም እምነት አባቶች ቆራጥ እርምጃ ተግባራዊ ሳይሆን የቀረ ሲሆን አሁንም በየቦታው ተከታተይ የሆነ እርምጃ ለመውሰድ አባቶቹ እየተንቀሳቀሱ መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል።

በተለይም ይህንኑ የትምህርት ሚኒስቴር ሕግ በመቃወም ሲገልፁ የነበሩ ሠለፊያ እና አልቅዱስ ጋዜጣ አዘጋጆች በወያኔ ደህንነት ኃይሎች ተይዘው ለእስር ከተዳረጉ በኋላ ምርመራዬን አልጨረስኩም በማለት የወያኔ ዓቃቤ ሕግና ዳኞች ጋዜጠኞቹን እያመላለሷቸው ከመሆኑም በላይ ባሉበት እስር ቤት ውስጥም ከፍተኛ ወከባ እየተደረገባቸው መሆኑን ምንጮቹ ገልፀው ይህ ሁሉ እርምጃ እየተወሰደባቸው ያለው በሼህ ኤልያስ ሬድዋን በፃፈው የትዕዛዝ ደብዳቤ መሆኑንም ምንጮቹ አጋልጠዋል።

አንድ የእስልምና እምነት ተከታይ የሕግ ባለሙያ እንደሚሉት ከሆነ አሁን በጋዜጠኞቹ ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ሕጋዊ ያልሆነ ያፈጠጠና ምንም አይነት መስመር ያልያዘ ነገር ግን የብቀላ እርምጃ መሆኑን በግልፅ ያሳየ ነው ሲሉ ገልፀው በአሁን ሰዓት ተከስሰው ፍ/ቤት ቀርበው ያሉት ጋዜጠኞች ወዲያው ጉዳዩ መታየት ሲገባው ምርመራዬን አልጨረስኩም እየተባለ በጊዜ ቀጠሮ የሚያንከራትቷቸው ከጋዜጣ ውጭ ምን ሌላ ማስረጃ ሊቀርብ ሆኖ ነው? ሲሉም ጥያቄ ያነሳሉ። ጮነዚሁ የታሰሩ ጋዜጠኞች ባለፈው ሳምንት የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም ፍ/ቤት ቀርበው ለየካቲት 28 ቀን 2000 ዓ.ም ተቀጥረው የነበረ ቢሆንም አሁን ለሌላ አንድ ሳምንት ጊዜ ቀጠሮ ተሰጥቷቸው ወደ እስር ቤት እንደተመለሱም ለማወቅ ተችሏል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በአሁን ሰዓት እብሪተኛው ወያኔ የጀመረው ወያኔያዊ ሴራው ያልተሳካለት ቢሆንም በትምህርት ቤት ተግባራዊ የሚሆን ያወጣውን ሕግ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ይመልከቱት በሚል ወደ የትምህርት ቤቱ ያስተላለፈ ሲሆን፣ እንደ አዲስ አሁን ሕጉን ይመልከቱ ይባል እንጂ በአዲስ አበባ ሁሉም ትምህርት ቤት ተግባራዊ እንዲደረግ ሐጉስ በተባለ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ግለሰብ አማካኝነት ደብዳቤ መፃፉ አይዘነጋም።

ወያኔ በሕዝቡ መካከል ከፍተኛ ግጭት እንዲከሰት ጥረት እያደረገ በደቡብ ክልል በርካታ ሰዎች ለሞት እየተዳረጉ ባለበት ወቅት ባለፈው ሳምንት በዲላ ተመሳሳይ ግጭት እንዲቀሰቀስ አድርጎ ሁለት የ3ኛ ዓመት ተማሪዎች በፌዴራል ፖሊስ የተገደሉ ሲሆን በዚሁ ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥም በአለማያ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ቀውስ እንዲፈጠር ማድረጉ ተጋለጠ።

የወያኔው ቡድን ሕዝቡን እርስ በእርስ እያጋጨ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲዳክር የነበረው ስልቱ ሲነቃበት በግዴታ ያለምንም ወንጀላቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎችን እያባረረ መሆኑን ከአለማያና ከዲላ ዩኒቨርስቲዎች የደረሰን ዘገባ ገለፀ።

ከአለማያ ዩኒቨርስቲ የደረሰን ዘገባ እንደሚገልፀው ከሆነ የካቲት 13 ቀን 2000ዓም «ተማሪዎች ዝምታን መርጠዋል» በሚል ፍራቻ የገባቸው የወያኔ ደህንነቶች እርስ በእርስ በብሔር እንዲጋጩ ለማድረግ አዲስ ስልት ወጥነው ተግባራዊ ሊያደርጉ ቢሞክሩም ጥቂት ተማሪዎች ቀድመው በማወቃቸውና ለግቢው ተማሪዎች ይህንኑ ይፋ በማድረጋቸው የተነሳ የወያኔ ደህንነቶች ያሰቡት ሳይሳካ እንደቀረ ገልጿል።

ይሁን እንጂ ይላል የደረሰን ዘገባ ይሁን እንጂ ደህንነቶቹ ከወያኔ አባል የዩኒቨርስቲው አስተዳደሮች ጋር በመሆን ተቃውሞ ልታነሱ ነበር በማለት ምስጢሩን አውቀው ያጋለጡትን 8 ተማሪዎች ከትምህርታቸው እንዲባረሩ ያደረጓቸው ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱ እድሜ ልካቸውን በሐገር ውስጥ በየትኛውም ዩኒቨርስቲ እንዳይማሩ እገዳ የተጣለባቸው መሆኑን አጋልጧል።

ወያኔ ከሕዝብ ጋር አይጥና ድመት ሆኖ ባለበትና ዙሪያውን እንደብራና ተወጥሮ ባለበት በዚህ ወቅት ተማሪዎች ዝም ማለታቸው ተንኮል አዝለው ነው በሚል ፍራቻ ብቻ እርስ በእርስ ለማጋጨት ሲያሴር ተነቅቶበት በማጋለጣቸው ከትምህርት ገበታቸው ማባረሩ የሚያሳዝንና የሚያንገበግብ መሆኑን የገለፁት የአለማያ የ3ኛ ዓመት ተማሪዎች ወያኔ ከገባበት ውጥረት ለመተንፈስ ሲል ብቻ ያሰበው ሲከሽፍበት በንዴት ይሄንን መሳይ ተግባር መፈፀሙ ሊገርመን አይገባም መጀመሪያስ ወያኔ ማን ነውና? ሲሉም በአንክሮ ሲጠይቁ ተደምጠል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በተመሳሳይ መልኩ በዲላ የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ.ም የወያኔ ደህንነቶች በተማሪዎች መካከል ፀብ እንዲፈጠር አድርገው በመሀሉም ገላጋይ መስለው የፌዴራል ፖሊስ እንዲገባ የወያኔ ተላላኪ የዩኒቨርስቲ አስተዳደሮች በማድረጋቸው በወሰደው የድብደባ እርምጃ ሁለት ተማሪዎች የሞቱ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ ትምህርት እስከዚህ ሳምንት ድረስ ያልተጀመረ ከመሆኑም በላይ የአይናችሁ ቀለም አለማረንም የተባሉ ንፁህ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው ላይ የተባረሩ መሆኑም ከዲላ የደረሰን ዘገባ አጋልጧል።

አሁንም ወያኔ ባለበት ውስጣዊና ውጫዊ ጭንቀት የተነሳ እንዲህ ያለ ተመሳሳይ እርምጃ በሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ሊወስድ እንደሚችልም ለደህንነት ቢሮ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ጠቅሰዋል።

በሌላ በኩል ሰሞኑን በአዲስ አበባ የወያኔ የጦሩ አባላት ከወትሮው በተለየ መልኩ ውጥረት ውስጥ ገብተው እንደነበረ ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

ከየካቲት 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በመከላከያ ሚኒስቴር ቢሮ፣ በማስታወቂያ ሚኒስቴር አካባቢ እና በላይኛው ቤተ መንግስት ዙሪያ ከወትሮው እንቅስቃሴ በተለየ መልኩ ቀይ ቆብ የደፉ ወታደሮች በልዩ ጥበቃ ከላይ ታች እያሉ በፓትሮል ጥበቃ ሲያደርጉ እንደነበረ የአይን እማኞች ገልፀው የተከሰተው ነገር ግን ምን እንደሆነ አልታወቀም ሲሉም ገልፀዋል።

ሰኞ የካቲት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በተመሳሳይ መልኩ ከዚህ በፊት አልፎ አልፎ ብቻ የሚከተፈው የላይኛው ቤተ መንግስት በሒልተን አቅጣጫ ያለው በር ተከፍቶ በሁለት ኦራል ቀይ ቆብ የደፉ ወታደሮች በፍጥነት በሸራተን ሆቴል አቅጣጫ ወደ መከላከያ ሚኒስቴር ሲከንፉ ተስተውሏል። ገሚሶቹ ከወትሮው በተለየ መልኩ ቤተ መንግስቱን ዙሪያውን በእያንዳንዱ ወታደር መሀል በ5 ሜትር ርቀት በመትረየስና በስናይፐር ጭምር ወጥረው መዋላቸውንም የአይን እማኞች ገልፀዋል።

የወያኔ ወታደሮች በአዲስ አበባ ላይ እንዲህ ያለ ውጥረት ውስጥ እና ወከባ ላይ ባሉበት ወቅት በመኮንኖች የስብሰባ አዳራሽ በከፍተኛ ወታደራዊ ጥበቃ ከፍተኛ መኮንኖች ስብሰባ መዋላቸውን ከመከላከያ የውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ገለፀ።

ማክሰኞ የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በዚሁ በመኮንኖች የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ የኮሎኔል ማዕረግ ያላቸውና የጄኔራል ማዕረግ ያላቸው ከፍተኛ መኮንኖች ከጧቱ 3 ሰዓት ጀምሮ እስከ 7 ሰዓት ድረስ በስብሰባ ተጠምደው እንደነበር ምንጮቹ ገልፀው በአሁን ሰዓት ወያኔ ዙሪያውን ተወጥሮ ባለበት ጉዳይ ለመነጋገር ሳይሆን እንዳልቀረም አስረድተዋል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በተለይ በአሁን ሰዓት በምስራቅ ከታጣቂ ተቃዋሚ ኃይል ጋር፣ በምዕራብ ከታጣቂ ተቃዋሚ ኃይል ጋር፣ በሰሜን ከሻዕቢያ ጋር እንደ ብራና ቆዳ ተወጥሮ ባለበትና የውጭ ሀገር መኮንኖችን በኮንትራት ቀጥሮ እስከማስገባት በደረሰበት ወቅት ጀኔራሎቹና ወሳኝ የሆኑ የሕወሓት ኮሎኔሎች በአንድነት በመኮንኖች ስብሰባ አዳራሽ ሲመክሩ የሰነበቱት በወቅታዊ ጉዳይ ላይ ሳይሆን እንዳልቀረ ምንጮቹ ግምታቸውን ሰንዝረው በአሁን ወቅትም በአዲስ አበባ መከላከያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ውስጥ ከፍተኛ ውጥረት ሰፍኖ እንደሚገኝ ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት በኦጋዴን በአንድ ተነጣይ የወያኔ ጦር ላይ ታጣቂዎች ድንገተኛ ጥቃት ሰንዝረው ከባድ ጉዳት አደረሱ ተብሎ በተነገረበት ወቅት በመከላከያ ሚኒስትር ከፍተኛ መኮንኖች ዘንድ የመደናገጥ ስሜት ተፈጥሮ እንደነበር ያስታወሱት ምንጮቹ አሁንም በተመሳሳይ መልኩ በምዕራብ በኩል ግዙፍ የጦር ኃይል እየተንጓዘ መሆኑን ሳይሸሽጉ ገልፀዋል፡፡

ወያኔ በደቡብ ምዕራብ በቤንሻንጉልና በጉንደር ውስጥ ከታጣቂ ተቃዋሚ ኃይል ጋር ጦርነት ሲያደርግ መሰንበቱን አርብ የካቲት 28 ቀን 2000 ዓ.ም ምሽት ላይ በዜና እወጃው ያረጋገጠ ሲሆን፣ ከስፍራው በደረሰን ዘገባ መሰረት ከማክሰኞ የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 27 ቀን 2000 ዓም ለተከታታይ ሶስት ቀናት ከባድ ውጊያ ተደርጎ በወያኔ ጦር ላይ ጉዳይ የደረሰበት ከመሆኑም በላይ በጦርነቱ ወቅት የጀትና የጦር ሂሊኮፕተሮች ተሳትፈው እንደነበረ የገለፀው የደረሰን ዘገባ ጦርነቱ ከእግረኛ አልፎ በአየር ጭምር መካሄዱ የታጣቂ ተቃዋሚዎች መጠንከርን ያሳየ ነው ሲል ዘገባው አስረድቷል፡፡ ምንም እንኳዋን ለተከታታይ ሶስት ቀናት ከባድ ውጊያ ተደርጎ በወያኔ ጦር ላይ ከፍተኛ ኪሣራ የደረሰ ቢሆንም ዝርዝሩን ለጊዜው ለማግኘት እንዳልተቻለ ዘገባው ጨምሮ ገልጿል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በጅቡቲ መስመር ከ300 ኪሎ ሜትር በላይ የውጊያ ቀጣና በሚል በወታደራዊ ኮንቮይ የነዳጅና የደረቅ ጭነት መመላለሻ መኪናዎች እየተንጓዙ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆ በአሁን ሰዓት ሀገሪቱ በሁሉም አቅጣጫ በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ እንደምትገኝ ያስገነዘበ ነው ሲል አስረድቷል፡፡

ማክሰኞ የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም መኮንኖች ክበብ ስብሰባ ካደረጉ ጀኔራሎች መካከል ጥቂቶቹ እንደገና ከምሽቱ 2 ሰዓት ቤተ መንግስት መለስ ጠርቷቸው እንዳነጋገራቸው የቤተ መንግስት ምንጮች ገለፁ፡፡

ሶሞራ የኑስ

ዮሐንስ ገ/መስቀል

ገብረ እግዚአብሔር መብርሀቶም



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ታደሰ ወረደ

ሞላ ኃ/ማርያም የተባሉት የሕወሓት ጄኔራሎችን መለስ በቤተ መንግስት ውስጥ ለሁለት ሰዓታት ያህል ያነጋገራቸው ሲሆን ለጊዜው በምን ጉዳይ ላይ እንደሆነ በትክክል ባይታወቅም በአሁን ሰዓት በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ጉንደር፣ በአፋር ክልል፣ በሰሜን ትግራይና በምስራቅ አጋዴን አካባቢ የተቃዋሚ ኃይሎችና ሻዕቢያ እንስቅቃሴ እያደረጉ በመሆኑ ከዚሁ ጋር በተገናኘ መልኩ ውይይት ለማድረግ ሳይሆን አይቀርም በማለት ምንጮቹ ግምታቸውን ሰንዝረዋል::

በሌላም በኩል በቅርቡ ከውጭ ሀገር የመጡ የውጭ ዜጋ የሆኑ መኮንኖች ተግባብተው እንዲሰሩ መመሪያ ከመለስ ለመቀበል እንደተሰባሰቡ ጠቁመው ምናልባትም የውጭ ሀገር መኮንኖቹ በመምጣታቸው የወያኔ መኮንኖች ደስተኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ተግባብተው እንዲሰሩ መመሪያና ትዕዛዝ ከመለስ ለመቀበል ሳይሆን እንዳልቀረም ያላቸውን ተጨማሪ ግምት አስፍረዋል::

ካላቸው እውቀትና ብቃት ውጭ በሕወሓት ታጋይነታቸው ብቻ የጄኔራልነት ማዕረግ ተሸክመው ለመለስ ታዛዥነታቸውን በመግለፅ የሚኖሩት እነዚሁ መኮንኖች በማዕረግ አነስተኛ በእውቀት ከእነሱ የበለጡ መኮንኖች በሰበብ አስባብ እንዲያባርሩ እና ከማዕረጋቸው ዝቅ እንዲሉና የሠራዊቱን አባላት እያንገላቱ እንደሚገኙም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

ልበ ድፍኑ የወያኔ ቡድን በጀመረው ሰንካላ አካሄድ ቀጥሎበት ኢትዮጵያን ወትሮም ለማፈራረስና ለመበተን ተግቶ እየሰራ መሆኑን ሰሞኑን በአድዋ በዓል ማግስት በሰራው አስነዋሪ ተግባሩ ማስመስከሩን ከአድዋ ከተማ የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

የወያኔው ቁንጮ ሰዩም መስፍንና የወያኔው የሽምግልና አባት የሚባለው ስብሀት ነጋ የካቲት 23 ቀን 2000 ዓ.ም በአድዋ ድል በዓል እለት አይመለከተንም በሚል በፕሮግራሙ ላይ ሳይገኙ ቀርቶ በማግስቱ የካቲት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በአድዋ ተገኝተው በአድዋ ድል ታላቅ ታሪክ የፈፀሙ ተብሎ የአንድ ግለሰብ ሀውልት ተሰርቶ መመረቃቸውን ይኸው ከአድዋ የደረሰን ዘገባ አጋለጠ::

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መስዋዕትነት የከፈለበትን የአድዋ ድል ለሕወሓት መወለድ መሰረት ናቸው የተባሉ ግለሰብ ለአድዋ መታሰቢያ ተብሎ በአደባባይ ሀውልታቸው እንዲተከል ያደረጉት ወያኔዎች ወትሮም የኢትዮጵያን ታሪክ ከፋሽስቱ ጣሊያን በበለጠ እያጉደፉና እያፈራረሱ የመጡ ከመሆኑም ባሻገር ታሪኩ በሙሉ የወያኔ ሕወሓት ብቻ እንዲሆንላቸው በማሰብ አሳፋሪና አሳዛኝ ታሪክ መፈፀማቸውን ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቷል::

የካቲት 23 ቀን 2000 ዓ.ም የአድዋ ድል በሚል ሲከበር አንድም የሕወሓት ባለሥልጣን ብቅ ያላለ ከመሆኑም ባሻገር የሌሎች ተለጣፊ ድርጅት ባለሥልጣናት



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ግን አድዋን አጨናንቀው የዋሉ መሆኑን ዘገባው ገልፆ ሁሉም ወደ መጣበት ተመልሶ በሄደበት ማግስት የሕወሓት ባለሥልጣናት ከመለስ በስተቀር ሁሉም በአድዋ ተገኝተው የአድዋ ድል በዓል መታሰቢያ በሚል የአውልአሉም የተባለ ግለሰብ ሐውልት መመረቃቸውን የደረሰን ዘገባ አስረድቷል።

በመጨረሻም ለወያኔ ከፍተኛ ጠቃሚ ሰው ነው ተብሎ በእነመለስ ጭምር ሲወደስ የነበረው የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል፣ የኦህዴድ ምክትል ሊቀመንበር፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ ግርማ ብሩ ማዕከላዊ ምርመራ ለ3ቀን ታስሮ እንደተፈታ የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ።

ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ ለጥያቄ ትፈለጋለህ በሚል ማዕከላዊ ምርመራ ቢሮ ተጠርቶ በዚያው ወደ ዘብጥያ ተወርውሮ የነበረው ግርማ ብሩ ለ3 ተከታታይ ቀናት ታስሮ ቃሉን ሰጥቶ በዋስ የተፈታ ሲሆን፣ ታስሮ የነበረው በሙስና ተጠርጥሮ እንደሆነም ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በሁሉም አቅጣጫ የሀገሪቷን ሐብት እንደ ቅርጫ ስጋ እየተቀራመቱ ሀብታቸውን እያደለቡ ያሉት የወያኔ ባለሥልጣናት በየፈርጁ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እያግበሰበሱ ሕዝቡን ለድህነት ሀገሪቷን ለምድረ በዳነት የዳረጓት ሲሆን አሁንም የበላችው ያገሣታል በላይ በላዩ ያጉርሣታል እንዲሉ እነ ግርማ ብሩና መሳዮቹ እስከዛሬ ድረስ ያካበቱት ሀብት አልበቃ ብሏቸው አሁን ደግሞ ከወርቅ መጭበርበር ጋር በተያያዘ ሙስና ፈፅመሃል ተብሎ መታሰሩ የወያኔ ባለሥልጣናት ምን ያህል ብልሹ እንደሆኑ ያረጋገጠ ነው ሲሉ እነዚሁ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል።

ባለው ስነ ምግባር ጨዋና በሳል ሰው ነው ተብሎ በነመለስ ጭምር ሲወደስ የነበረው ግርማ ብሩ የኦህዴድ ምክትል ሊቀመንበር የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ሆኖ ከፍተኛ ስልጣን ይዞ ተራ ማጭበርበር ውስጥ ገብቶ ተገኝቷል ተብሎ ለእስር መዳረጉ የወያኔ ባለሥልጣናት ከላይ እስከታች ድረስ በሙስና የተጨማለቁና ምግባር የሌላቸው አስነዋሪዎች ናቸው ሲሉም የማዕከላዊ ምርመራ ምንጮቻችን ገልፀዋል።

ሌሎች ወገኖች እንደሚሉት ደግሞ ሙስና ከተባለማ ከሕወሓት ባለሥልጣናት ከመለስ ጀምሮ ያሉት መጠየቅ ነበረባቸው እንጂ እነዚህማ እንዴት ሊሆን ይችላል በማለት ጠይቀው በተለይ የሕወሓት ባለሥልጣናት በረሃ የደማንበት፣ የቆሰልንበትና መሥዋዕትነት የከፈልንበት ነው በማለት ቀን በብርሃን፣ ማታ በጨለማ የሕዝቡን ሐብትና ንብረት ዘርፈው ሚሊኒየር የሆኑት ሳይጠይቁ እነ ግርማ በፍፁም ሊጠየቁ አይገባም። ምናልባትም በአሁን ሰዓት ብአዴንና ኦህዴድ ከሕወሓት ጋር ክፍተት



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

**የፈጠሩ በመሆናቸው ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሰበብ ተፈልጐባቸው ይሆናል ሲሉ ግምታቸውን ሰንዝረዋል።**

**ዘግይቶ በደረሰን ዘገባ መሠረት ግርማ ብሩ ከማዕከላዊ ለ3 ቀን ቆይቶ ከወጣ በኋላ ወደ ቤቱ ሳይሆን ወደ ቃሊቲ እስር ቤት እንደገባ ምንጮቹ ገልፀዋል።**



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com